# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ትንሣኤ በዋለ በአምስተኛው ሰንበት የሚከናወን ሥርዓተ አምልኮ

ዘመነ ትንሣኤ ወይም ፋሲካ የሚባለው ከጌታችን ትንሣኤ ጀምሮ እስከ ዕርገት ያሉት ቀኖች ናቸው። በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመሩት መዝሙራት ሞትን ትንሣኤን ስቅለትን የመሳሰሉትን የሚያነሱ ናቸው።

## የዕለቱ ምስባክ

በልው ወጸግቡ ጥቀ
ወወሀቦሙ ለፍትወቶሙ
ወኢያህጥኦሙ እምዘፈቀዱ

በሉ እጅግም ጠገቡ
ምኞታቸውንም ሰጣቸው
ከወደዱትም አላሳጣቸውም

መዝ ፸፯፥፳፱

ወንጌል፥ ዮሐ ፳፩፥፩-፲፭
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

«ፋሲካ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| ፩ | ሮሜ ፬፥፲፬-እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| ፪ | ራዕ ፳፥፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| ፫ | የሐዋ ሥራ ፲፥፴፱-፵፬ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### «ፋሲካ»

በዕብራይስጥ ፋሲካ «ፓሳሕ» ይባላል። በኦሪት ዘጽአት ምዕራፍ ፲፪ እንደምናነበው የእስራኤል ልጆች ፋሲካን ያዘጋጁት አስረኛ መቅሰፍት ሆኖ በታዘዘው ሞተ-በኵር በግብጻውያን ላይ ሲያልፍ እነሱንም የሞት መልአክ እንዳይቀጣቸው ሞት እንዲያልፋቸው የፋሲካውን በግ አርደው ያከበሩት የእግዚአብሔር በዓል ነው። ፋሲካን ያከበሩት ከነጻነት በፊት ሲሆን ለሁለት ዓላማ ነበር ያከበሩት፥
፩) ከእግዚአብሔር ፍርድ ለመዳን
፪) ሊያጠፋ ከመጣው አጥፊ መልአከ ሞት ለመዳን ነበር።

በዓሉንም ከነጻነት በኋላ በየአመቱ በአሥራ አራተኛው ቀን ያከብሩት ነበር (ዘጸ ፲፮፥፲፮ ። ዘጸ ፲፪፥፩-፫) ከዚያም እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የቦካውን ነገር ለመብላት ስላልተፈቀደላቸው አንድ ሳምንትም የቂጣ በዓልን ያከብራሉ።

ያልቦካ መብላት፥
፩) የእስራኤል በችኮላ ከባርነት መላቀቅ
፪) ከኃጢአት ኑሮ የመላቀቅ ከባርነት ኑሮ የመለየት ምሳሌ ነበር (ዘጸ ፲፪፥፲፰-፳ ፴፫-፴፬ ። ዘዳ ፲፮፥፩-፫)

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የፋሲካ ሳምንት ነበር (ሉቃ ፳፪፥፲፬-፲፮ ። ዮሐ ፲፰፥፴፰-፵) ክርስቶስ ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስላፈሰሰልን «ፋሲካችን ክርስቶስ» ተባለ ፩ኛ ቆሮ ፭፥፯ ። ፩ጴጥ ፩፥፲፰-፲፱)። ስለዚህ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓለ ፋሲካ ተብሎ ይጠራል። በአጠቃላይ ፋሲካ ማለት መሻገር ማለት ነው። ይህ ዘመን ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገርንበት፣ ከሐሳር ወደ ክብር ያለፍንበት፣ ከድካም ወደ ኃይል ያለፍንበት ዘመን ነው። በትንሣኤ እረፍተ መንግሥተ ሰማያትን የምንወርስበትን ሞት ፈርኦን የተሻረበት የዲያቢሎስ ግብጻዊ የበኵር ልጆቹ ሞት፣ ሐዘን፣ ልቅሶ፣ ትካዜ፣ ድካም፣ መቃብር በሞት የተቀጡበት ዘመን ነው። እስራኤል ዘነፍስ ምእመናን ወደ ከነአን መንግሥተ ሰማያት ያለፉበት፤ ቀይ ባህር ኃጢአት በክርስቶስ የተከፈለበት፤ መና ሕይወት ከሰማይ ለምእመናን የወረደበት፤ ጥል የወደቀበት አምደ ብርሃን ክርስቶስ በሕዝቡ መካከል እያበራ የሕዝብ ብርሃን ሆኖ የሚገለጥበት፤ አንድ መንጋ በአንድ እረኛ የሚመራበት ዘመን ነው።

በዚህ የፋሲካ ወቅት የምናከብረው ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገርንበትን ፋሲካችንን ክርስቶስ ነው የምናከብረው። በክርስቶስ ወደ ሕይወት አልፈንበታል፤ ሞትን ተሻግረንበታል፣ ፍርድን አሸንፈንበታል። «እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይወጣም» (ዮሐ ፭፥፳፬) ብሎ እንዳስተማረን ክርስቶስ ፋሲካችን ማእዶታችን ነው።

### የበዓሉን ምስጢር ከሚገልጹ የቅዱስ ያሬድ የመዝሙር ክፍሎች

*በግዕዝ፥*
«ፋሲካ ዛቲ እለት ቅድስት ይእቲ (አዝ) ዛቲ እለት ንትፌሳሕ በቲ (አዝ) ዛቲ እለት ናሕይ ወእረፍት (አዝ) ሰማይ ወምድር ይትፌስሑ በቲ (አዝ) ፋሲካ ፋሲካ ፋሲካ ተዘከረ ትንሣኤሁ ለመድኃኒነ»
*አማርኛ፥*
ይህች የፋሲካ ዕለት ቅድስት ናት (አዝ) በዚህ ዕለት እንደሰትባት (አዝ) ሰማይና ምድር በሷ ደስ ይላቸዋል (አዝ) ፋሲካ ፋሲካ ፋሲካ የመድኃኒታችን ትንሣኤ መታሰቢያ

---

*በግዕዝ፥*
ንጉሠ ዓለም መንስኤ ሙታን ተንስአ በሣልስት ዕለት
ሰንበተ ክርስቲያን ተንስአ ክርስቶስ እሙታን
*አማርኛ፥*
የዓለም ንጉሥ የሙታን ትንሣኤ ክርስቶስ በሦስተኛው ዕለት ተነሳ በሰንበት ክርስቲያን ክርስቶስ ከሙታን ተነሳ (አርባዕት)

---

*በግዕዝ፥*
ንግበር በዓለ በትፍስሕት ቅድስት ፋሲካ በሐሴት እስመ ለስሐ ሕምዙ ለሞት ወተቀጥቀጠ አርዑተ ኃጢአት
*አማርኛ፥*
በደስታና በሐሴት የቅድስት ፋሲካን በዓል እናክብር የሞት መርዝ ተሽሮአልና የኃጢአትም ቀንበር ተቀጥቅጦአልና።

---

*በግዕዝ፥*
ትንሣኤሁ ገብረ በሰንበት ወሰበረ ኆኃተብርት
እግዚአ ለሰንበት ሲኦለ ወረደ በነደ እሳት ተቤዘወሙ ለቀደምት
*አማርኛ፥*
ትንሣኤውን በሰንበት አደረገ፤ የሰንበት ጌታ የብረት በሮችን ሰበረ ሲኦል ወርዶ በነደ እሳት የነበሩትን የቀደሙትን አባቶች ተቤዣቸው። (ዓራራይ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM